**BIF Beratungsstelle für Frauen**
gegen Gewalt in Ehe und Partnerschaft

Tel. 044 278 99 99
bif-frauenberatung.ch

AM*

# በመፋታት ወይም በመለያየት ላይ ላሉ ሴቶች የሚጠቅም መረጃ፡

## በህጋዊ ትዳር ላይ ላሉ
## በተመሳሳይ የጾታ ግንኙነት ውስጥ
## ተፈራርመው አብረው ለሚኖሩ
## ሳይጋቡ አብረው ለሚኖሩ

* ይህንን መረጃ በተለያዩ 16 ቋንቋዎች ማግኘት ይቻላል፡

„የሚደርስብኝ በደል እንዲያበቃና እንድከበር እፈልጋለሁ“

ማውጫ


መለያየት እፈልጋለሁ ምን ማድረግ አለብኝ? 3

የትዳር ጉዳይና ጥበቃ ፍርድ ቤት ምን ያህል ያስከፍላል ?
የጠበቃን ወጪ የሚሸፍነው ማን ነው ? 3

የትዳር ጉዳይና ጥበቃ ፍርድ ቤት የሚዳኝባቸው ነጥቦች የትኞቹ ናቸው? 3

ባለቤቴ መለያየት መፈለጌን ሲሰማ ሊያደርግ የሚችለውን ሁኔታ ሳስበው ያስፈራኛል 3

መለያየቱ በፍጥነት መሆን ካለበት 3

ቤቱ ውስጥ ሊቆይ የሚችለው ማን ነው ? 3

ልጆቹ መኖር ያለባቸው ከማን ጋር ነው? 3

ባለቤቴ ልጆቹን ሊጎበኝ የሚችለው በየስንት ጊዜው ነው ? 4

በምን እንተዳደር ? 4

መለያየቴ በመኖሪያ ፈቃዴ ላይ የሚያመጣው ተጽእኖ አለ ወይ? 4

የትዳር ጉዳይና ጥበቃ ፍርድ ቤት የሚደረገው ስምምነት ወይም
የሚኖረው ሁኔታ ምን ይመስላል? 4

በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ካልተስማማሁ ምን ማድረግ እችላለሁ? 4

በአስቸኳይ ወድያውኑ መፋታት አይሻለኝምን? 5

የማልፈልገውን ጋብቻ እንድፈጽም ከተገደድኩኝ ምን ማድረግ እችላለሁ? 5

ከተመሳሳይ ጾታ ጋር በፍቅር ግንኙነት ላይ የተደረገን ህጋዊ ስምምነት ለማፍረስ ምን
ማድረግ አለብኝ? 5

ከፍቅረኛዬ ጋር ትዳር ሳንመሰርት አንድ ላይ እንኖራለን፣ አሁን ግን መለያየት እፈልጋለሁ
(ኮንኩቢናት) 5

አስፈላጊ አድራሻዎች 5

አዘጋጅ 6

## መለያየት እፈልጋለሁ ምን ማድረግ አለብኝ?

በመኖሪያ አካባቢሽ ወደሚገኘው ጉዳዩ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት (www.gerichte-zh.ch) የትዳር ጉዳይና ጥበቃ ሂደት (Formular Eheschutzverfahren) በመጀመር ተለያይተሽ እንድትኖሪ ማመልከት ትችያለሽ (ከጋብቻ ጥበቃ ጉዳይ የሚሰጥ ፎርም) ጉዳይሽን እራስሽ ወይም በጠበቃሽ በኩል ማቅረብ ትችያለሽ። ከፍርድቤቱ ጋር ወይንም ከጠበቃሽ ጋር በጉዳዩ ለመነጋገር በሚኖርሽ የመጀመሪያ ቀጠሮ ቢቻል ከዚህ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ይዘሽ ቅረቢ ።

- ገንዘብን በተመለከተ አሁን ያለሽበትን የገቢና ወጪ ሁኔታ የሚያሳዩ ሰነዶችን ፤ ላለፉት ሁለት አመታት ቀረጥ የከፈልሽበትን የሚያሳይ ክቀረጥ ቢሮ የተሰጠሽን ማስረጃ ፤ የቀረጥ ወረቀቶችን ፤ ለቀረጥ የሚጠቅሙ ፋክቱሮችን ፤ ክ 3 - 6 ወር ያለዉን የደሞዝ ወረቀት ፤ የወጪ ወረቀቶችን ፤ እስከ 3 ወር ድረስ ያለውን የወጪና የገቢ ዝርዝር የሚያሳይ የባንክ ደብተር ወይም ዶክመንት ።
- ባሳለፍሽዉ የትዳር ህይወት ዉስጥ የደረሰብሽን በደል የሚያሳይ ማንኛውንም ማስረጃ ። (ለምሳሌ ባለቤትሽ ያደረሰብሽን ጉዳት የሚገልጽ የሃኪም ማስረጃ ፤ የፖሊስ ማስረጃ ፤የቅጣት ወረቀት)

## የትዳር ጉዳይና ጥበቃ ፍርድ ቤት ምን ያህል ያስከፍላል ? የጠበቃን ወጪ የሚሸፍነው ማን ነው ?

አነስተኛ የገቢ መጠን ካለሽ አንቺ ወይም ጠበቃሽ ያለገንዘብ ጉዳዩ እንዲታይልሽ እንዲሁም በነጻ አገልግሎት የምትሰጥ ጠበቃ እንድትቆምልሽ ማመልከት አለብሽ። (ማመልከቻ) ይህ ከተፈቀደልሽ የፍርድ ቤቱንም ሆነ የጠበቃዋን ወጪ መንግስት ለጊዜው ይሸፍናል። ለወደፊቱ የተሻለ ገቢ የሚኖርሽ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የፍርድ ቤቱንና የጠበቃሽን ወጪ በ 10 አመት ጊዜ ውስጥ እንድትከፍይ ይጠብቅብሻል (ማብራሪያ ወረቀት ) አሁን ባለሽ የገንዘብ አቅም ራስሽ ልትከፍዪ የምትችዪ ከሆነ ደግሞ ይህ የቤተሰብ ፍርድ ቤት ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቅ ከምክር አገልግሎት ቢሮ ወይም ከጠበቃሽ መረጃ ማግኘት ትችያለሽ።

## የትዳር ጉዳይና ጥበቃ ፍርድ ቤት የሚዳኝባቸው ነጥቦች የትኞቹ ናቸው?

የትዳር ጉዳይና ጥበቃ ዳኛዋ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ውሳኔ ታሳልፋለች

- የመኖሪያ ቤት ውስጥ ማን እንደሚቆይ
- ልጆቹ ከማን ጋር መኖር እንዳለባቸው
- ሌላኛው ወላጅ ልጆቹን መቼ ማየት እንዳለበት
- ለመተዳደርያ የሚሆነውን ወጪና ገቢን በተመለከተ
- ከመለያየት በሁዋላ የሚገኘውን ንብረት የጋራ እንዳልሆነ

## ባለቤቱ መለያየት መፈለጌን ሲሰማ ሊያደርግ የሚችለውን ሁኔታ ሳስበው ያስፈራኛል

ባለቤትሽ በአንቺና በልጆቹ ላይ በደል ይፈጽማል? ወይም ያስፈራራችዋል?
ፖሊስ በጉዳዩ ጣልቃ በመግባት ጥበቃ ሊያደርግላችሁ ይችላል:: (GSG Broschüre) (ስለ ደህንነት በራሪ ወረቀት) ባለቤትሽ ከቤት እንዲወጣ ይደረጋል፡ ወደ ቤት እንዳይመጣና ወዳላችሁብት አካባቢም እንዳይደርስ ካንቺም ሆነ ከልጆቹ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንዳያደርግ ለ 14 ቀን ይታገዳል። አስፈላጊ ከሆነም በ 8 ቀን ውስጥ ይሄ ጥበቃ ለአንድ ጊዜ ብቻ ወደ 3 ወር እንዲራዘም ማስደረግ ትችያለሽ (www.ist.zh.ch) ለተጎጅዎች የምክር አገልግሎት የሚሰጠው ተቋም(Opferberatungsstellen) በነጻና በታማኝነት እርዳታና የምክር አግልግሎት ያደርግልሻል።እነዚህ 3 ወራት ህጋዊ መለያየት ለማድረግ በቂ ናቸው ።በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሽ ባለቤትሽ ዛቻና ማስፈራሪያ ያደርግብኛል ብለሽ ከፈራሽ አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግልሽና ባለቤትሽ አንቺ ወዳለሽበት እንዳይቀርብ የሚያደርግ ህግ ለፍርድቤት ማመልከት ትችያለሽ። (በግለሰብ ደረጃ ህጋዊ የጥበቃ መብት (የፍታብሄር ህግ ቁ. 28 ለ) አስፈላጊ ሆኖ ካገኘሽው ለመለያየት ስታመለክቺ ይሄንንም የዕገዳ ጥያቄ አብረሽ ማመልከት ትችያለሽ። ይሄን በተመለከተ ከኛ ጋር ወይንም ከጠበቃሽ ጋር ልትነጋገሪና ምን አይነት አማራጮች እንዳለሽ ለማየት ትችያለሽ ። ባለቤትሽ ወዳንቺ እንዳይቀርብ የተሰጠውን ትእዛዝ ተላልፎ ሊያጠቃኝ ይችላል የሚል ፍርሃት ካለሽ፣ በትዳር ጓደኞቻቸው የተጠቁን ሴቶች ደህንነት የሚጠብቅና አስተማማኝ ማቆያ ቦታ ያለውን የሴቶች ቤት በመባል የሚታወቀውን ተቋም ማለትም (www.frauen-haus-schweiz.ch) ብትገናኚ ሊረዱሽ ዝግጁዎች ናቸው።

## መለያየቱ በፍጥነት መሆን ካለበት

ከትዳር ጉዳይና ጥበቃ ፍርድ ቤት ጊዜያዊ የሆነ መለያየት መጠየቅ ይቻላል። ይህንንም ለማድረግ የደረሰብሽን በደል የሚያመለክቱ ማስረጃዎችና አስቸኳይነቱን ሊያሳይ የሚችል ማስረጃም ማቅረብ ይኖርብሻል። ፍርድ ቤቱም በሰጠሻቸው ማስረጃዎች ላይ በመመርኮዝ ጊዜያዊና በፍጥነት ሊተገበሩ የሚችሉ መመሪያዎችን ይሰጣል። ከላይ የተጠቀሰውን አማራጭ መጠቀም ከፈለግሽ፣ ሂደቱና ስራው ብዙ ስለሆነ ከጠበቃ ወይም ለተበዳዮች እርዳታ ከሚሰጡ ድርጅቶች መማከር ያስፈልግሻል።

## ቤቱ ውስጥ ሊቆይ የሚችለው ማን ነው ?

በህጉ መሰረት ቤቱ ውስጥ ሊቆይ የሚገባው፣ ልጆቹን እንዲንከባከብ የተወሰነለት ከወላጆቹ አንዱ አካል ነው። በትዳር በኖራችሁበት ቤት ውስጥ መቆየት ከፈለግሽ፣ የሚከተሉትን ነገሮች በማመልከቻ መጠየቅ ትችያለሽ ፣

- በህጉ መሰረት ቤቱ ውስጥ ሊቆይ የሚገባው፣ ልጆቹን እንዲንከባከብ የተወሰነለት ከወላጆቹ አንዱ አካል ነው። በትዳር በኖራችሁበት ቤት ውስጥ መቆየት ከፈለግሽ፣ የሚከተሉትን ነገሮች በማመልከቻ መጠየቅ ትችያለሽ ፣
- ያለአንቺ እውቅና ባለቤትሽ ቤት ውስጥ እንዳይገባ፣ ሁሉንም የቤቱን ቁልፎች መመለስ አለበት። ሆኖም ባለቤትሽ ሁሉንም ቁልፎች አልመለሰም የሚል ጥርጣሬ ካለሽና ፍርሃት የሚሰማሽ ከሆነ ፣ የቤቱን የቁልፍ ጋንና ቁልፎቹን ማስቀየር ትችያለሽ።

## ልጆቹ መኖር ያለባቸው ከማን ጋር ነው?

እስካሁን ልጆቹን በይበልጥ ይንከባከብ ከነበረው ወላጅና ወደፊትም በዚሁ ሁኔታ ሊቀጥል ከሚችለው ወላጅ ጋር ነው። ዳኛዋ ለልጆቹ እድገት የተሻለውን ወላጅ ለመወሰን የራሷን ምርመራ ታደርጋለች። ባጠቃላይ ወንድምና እህቶች በፍጹም

መለያየት የለባቸውም። በውሳኔው ሂደት ላይ እድሜያቸው በአማካይ 6 አመትና ከዚያም በላይ የሆናቸው ልጆችም ሃሳብ ይካተታል።

## ባለቤቴ ልጆቹን ሊጎበኝ የሚችለው በየስንት ጊዜው ነው ?

ከልጆቹ ጋር አንድ ቤት ውስጥ የማይኖረው ወላጅ ልጆቹን የማግኘትና የማየት መብት አለው። ስለዚህም ከባለቤትሽ ጋር አንድ ስምምነት ማድረግና ለዳኛዋ ማሳወቅ አለብሽ። በሃሳብ የማትስማሙ ከሆነ ፣ ዳኛዋ ትወስናለች። በተለይ ደግሞ ልጆቹ መዋእለ ህጻናት የሚሄዱ ከሆነ በወር 2 ቅዳሜዎች ወይም እሁዶች ፣ ትምህርት ቤት ለሚሄዱ ልጆች ደግሞ 2 ቅዳሜና እሁድ በወር እንደዚሁም በአመት ውስጥ ትምህርት ቤት ለእረፍት ሲዘጋ 2 ሳምንት ካባታቸው ጋር ማሳለፍ ይችላሉ።

ልጆቹን የምትቀባበሉበት ሰአት በጥብቅ መከበር እንዳለበት ማወቅ አለብሽ። እንዲሁም በተለያዩ የበአል ቀናቶች ለፋሲካ ፣ ለጰራቅሊጦስ ፣ ወይም ለገና በቅድሚያ ስምምነት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ባለቤትሽ ልጆቹን የሚመታቸውና የሚያስፈራራቸው ከሆነ ወይንም ልጆቹ በሄዱ ቁጥር ሁከትና ችግር የሚፈጥር ከሆነ በሚመጣበት ጊዜ ከአጃቢ ጋር እንዲመጣና በመሃከላችሁ የሚያስማማችሁ ሰው እንዲመደብላችሁ መጠየቅ ትችያለሽ። ልጆቹን ሁልጊዜ ባጃቢ እንዲያይ የሚደረገው ግን ለልጆቹ ደህንነት በጣም አስጊ ከሆነ ብቻ ነው።

## በምን እንተዳደር ?

ፍርድ ቤቱ ለመተዳደሪያ የሚሆንሽን ገንዘብ እስኪወስንልሽ ድረስ ሳምንታት ወይንም ወራት ሊወስድ ይችላል፡ በመሆኑም ለመተዳደሪያ የሚሆን በቂ ገንዘብ ከሌለሽ ለጥንቃቄ ሲባል ለመንግስት ድጎማ ቢሮ ጥያቄሽን ማቅረብ አለብሽ። ከመንግስት የገንዘብ እርዳታ የማግኘት መብት አለሽ።

ከባለቤትሽ ጋር የጋራ የባንክ ደብተር ወይም ክሬዲት ካርድ ካላቹ ፡

- በተጨማሪም የባንክ ደብተሩ ወይም ክሬዲት ካርድ ካርዱ በባለቤትሽ ስም ከሆነ እንዲሁም እጅሽ ላይ በቂ ገንዘብ ከሌለሽ ለ 3 ወር ያህል የሚበቃሽን ገንዘብ በአስቸኳይ አውጪ።
- የባንክ ደብተሩ ወይም ክሬዲት ካርድ ባንቺ ስም ከሆነ ደግሞ ባለቤትሽ በካርዱ እንዳይጠቀም በአሰቸኳይ ማዘጋት አለብሽ።

ጉዳዩን የሚያየው የትዳር ጉዳይና ጥበቃ ፍርድ ቤት የሁለታችሁንም ገቢ አጣርቶ ላንቺና ለልጆቹ መተዳደሪያ የሚሆነውን ገንዘብ ይወስናል:: ሆኖም የተወሰነልሽ መተዳደሪያ ገንዘብ የማይበቃሽ ከሆነ ድጎማ ለሚሰጠው የመንግስት አካል(ሶሲያል)መጠየቅ ትችያለሽ።

እንደሁኔታው ደግሞ የምትሰሪ ከነበር ለስራ አጥ ቢሮ በማመልከት እንዲከፈልሽ መጠየቅ ትችያለሽ።

ፍርድቤቱ በወሰነው መሰረት መንግስት ለ አንድ ልጅ ቢበዛ እስከ 940ፍራንክ ሊከፍል ይችላል። ይሁን እንጂ ይሄ ድጎማ ሴቶችን የሚመለከት አይደለም።

የሚሰጥሽ መተዳደሪያ በትክክል እንደሚከፈልሽ የምትኖሪበት ቀበሌ መከታተል አለበት ይሄ ገንዘብ በትክክል ካልተከፈለ የሚከፍለውን አካል ቀበሌው ማስገደድ ይችላል።

## መለያየቴ በመኖሪያ ፈቃዴ ላይ የሚያመጣው ተጽእኖ አለ ወይ?

አብዛኛውን ጊዜ ስዊዘርላንድ ውስጥ በጋብቻ ወረቀት ያገኘ ሰው የመኖሪያ ፍቃዱ የሚሰራው ከባለቤቱ ጋር በትዳር አብሮ እስካለ ድረስ ብቻ ነው።(ቢ የመኖሪያ ፍቃድ) ስዊዘርላንድ ለመኖር የተሻለ መመዘኛና እድል ላላቸው የአውሮፓ ህብረት ዜጎች ግን ህጉ ልዩነት አለው። የአውሮፓ ዜግነት ለሌላቸው ሰዎች ከትዳራቸው ሲለያዩ ፈቃዳቸውን ለማራዘም የሚችሉበት መንገድ አለ፡ ይኸውም ከሶስት አመት በላይ ስዊዘርላንድ ውስጥ በትዳር የቆዩና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ባህሉን፣ ቋንቋውንና ወዘተ… የለመዱ ከሆኑ(ኢንተግሬት ያረጉ)ከሆኑ፣ እንዲሁም አሳማኝ የሆነ የግል ምክንያት በማቅረብ ፈቃዳቸውን ማሳደስ ይችላሉ ።በተለይም በትዳራቸው ላይ የደረሰባቸው በደል ካለ እንዲሁም ወደ አገራቸው መመለሳቸው አደጋ ላይ የሚጥላቸው ከሆነ ነው። በተለይ ደግሞ በባለቤትሽ ተበድለሽ ከሆነና ጉዳት ደርሶብሽ ከሆነ በተቻለሽ መጠን የሀኪም ወረቀቶችን፣ ከሴቶች ጥበቃ ቤት፣ ወይም ከምክር አገልግሎት ተቋማት፣በደልሽን በሚመለከት የተሰጠሽ ወረቀት ካለ፣እንዲሁም ከፖሊስ የተሰጠሽ ማንኛውም አይነት ማስረጃ ካለሽ በጥንቃቄ ማስቀመጥ አለብሽ። የመኖሪያ ፈቃድሽን እንዳትነጠቂ በመስጋት ብቻ በደል እየደረሰብሽ ቤት ውስጥ መቀመጥ የለብሽም። ይህን በተመለከተ በነጻና በታማኝነት የምክር አገልግሎት ልንሰጥሽ እንችላለን።

## የትዳር ጉዳይና ጥበቃ ፍርድ ቤት የሚደረገው ስምምነት ወይም የሚኖረው ሁኔታ ምን ይመስላል?

በቤተሰብ ጉዳይና በትዳር ጥበቃ ፍርድ ቤት የትዳር ጉዳይና ጥበቃ ፍርድቤት

ያለውን ሂደት በተመለከተ ከምክር አገልግሎት ተቋም ወይም ከጠበቃ ወይም ከፍርድ ቤት መረጃ ማግኘት ትችያለሽ። ወደ ፍርድ የምትሄጂው ያለጠበቃ ከሆነ

- እርግጠኛ ያልሆንሽበትን ስምምነት ሁሉ እንዳትፈርሚ፣ ወይም
- የምትፈርሚ ከሆነ በ 10 ቀን ውስጥ ውሳኔሽን መቀልበስ መቻልሽን አረጋግጪ፣ ከዛም ውሳኔውን ለአንዲት ጠበቃ አሳዪና ስምምነቱ አንቺን የሚጠቅም ካልሆነ በተባለው 10 ቀን ውስጥ ሃሳብሽን መቀየርሽን ለፍርድቤቱ አሳውቂ።

ልጆችን ወደዚህ ፍርድ ቤት ይዞ መምጣት ክልክል ነው ስለሆነም ጉዳይሽን ተረጋግተሽ እንድትጨርሺ ልጆችሽን ለግማሽ ቀን የሚይዝልሽ ሰው ብታዘጋጂ መልካም ነው።

የጀርመንኛ ቋንቋ በደንብ የማትናገሪና የማትረጂ ከሆነ ቀደም ብለሽ አስተርጓሚ እንዲመደብልሽ ጠይቂ።

## በፍርድቤቱ ውሳኔ ካልተስማማሁ ምን ማድረግ እችላለሁ?

በፍርድቤቱ ውሳኔ የማትስማሚ ከሆነ በ 10 ቀን ውስጥ ውሳኔ የተወሰነበትን ምክንያት ወይም ይግባኝ መጠየቅ ትችያለሽ። (በውሳኔው ወረቀት መጨረሻ ላይ ካልተማማሽ ያለሽ ህጋዊ መብት ይጻፋል)በ 10 ቀን ውስጥ ምንም አይነት ተቃውሞ ካላቀረብሽ ውሳኔው ይጸናል። ውሳኔው እንዲቀየር መጠየቅ የምትችዪው የተለየ አስገዳጅ ሁኔታ ከገጠመሽ ብቻ ነው።

ከባለቤትሽ ጋር ተመልሰሽ አብረሽ መኖር ከፈልግሽ ውሳኔው ከ3-5 ባሉት ሳምንታት ውስጥ በራሱ ይሻራል።

### በአስቸኳይ ወድያውኑ መፋታት አይሻለኝምን?

ሁለታችሁም ለመፋታት ከተስማማችሁና ለፍርድቤቱ ካረጋገጣችሁ ፍቺውን በማንኛውም ጊዜ ማድረግ ይቻላል። ነገር ግን ከልምድ እንደሚታየው ሰዎች ለመፈታት ፍርድቤትን ከጠየቁ በኋላ ሃሳባቸውን ይቀይራሉ ።በመሆኑም የመተዳደሪያውን ሁኔታ፣ የልጆቹን ሃላፊነትና የመኖሪያ ቤቱን በተመለከተ ለመወሰን ወደ የቤተሰብ ጉዳይና የጋብቻ ጥበቃ ፍርድ ቤት መሄዱ ሂደቱን ያቀለዋል። ከባለትዳሮቹ አንደኛው ቶሎ ለመፋታት የማይስማማ ከሆነ በህጉ መሰረት ሁለት አመት መጠበቅ አለባቸው። ነገር ግን አብሮ የመኖራቸው ተስፋ ያከተመለት ከሆነና አንዱ ወገን ባቀረበው የፍቺ ጥያቄ መፋታት ይችላሉ። ይሁን እንጂ ሂደቱ በጣም ከባድና ውስብስብ ነው ሚሆነው። ነገር ግን የፍቺው ጥያቄ ተቀባይነት ካላገኘ የፍርድ ቤት ሂደቱ በጣም ረጅም ጊዜ ይወስዳል። ለማንኛውም ከምክር አገልግሎት ተቋም ወይም ከ አንዲት ጠበቃ ወይም የፍርድ ቤት ምክርን ጠይቂ።

### የማልፈልገውን ጋብቻ እንድፈጽም ከተገደድኩኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?

ስዊዘርላንድ ውስጥ የሚኖር ሰው ሁሉ ነጻ የሆነ የትዳር ምርጫ የማድረግ መብት አለው። የስዊዘርላንድ ህግ በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጪ የሚደረገውን የግዴታ ጋብቻን የሚቃወም ነው።
አስፈላጊ ከሆነ ይሄንን ድህረገጽ መመልከት ትችያለሽ.(www.zwangsheirat.ch) ወይንም ከኛ ጋር መገናኘት ትችያለሽ። ነጻ የሆነ የምክር አገልግሎት የሚሰጥሽና በተለያየ ቋንቋ የሚያግዝሽ ሰው ይመደብልሻል።

### ከተመሳሳይ ጾታ ጋር በፍቅር ግንኙነት ላይ የተደረገን ህጋዊ ስምምነት ለማፍረስ ምን ማድረግ አለብኝ?

ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ጥንዶች ግንኙነታቸውን በህጋዊ መንገድ አስመዝግበው መብታቸውንና ግዴታቸውን በማውቅ ተከባብረውና ተጣምረው በአንድነት መኖር ይችላሉ። አብራሽ ከምትኖረው የፍቅር አጋርሽ በደል ወይም ማስፈራራት የሚደርስብሽ ከሆነ ፖሊስ ባለው ተበዳዮችን የመከላከል ስልጣንና ሃላፊነት መሰረት ጉዳዩን እንዲከታተልና ጥበቃ እንዲያደርግልሽ መጠየቅ ትችያለሽ።(GSG በራሪ ወረቀት)
እንዲሁም በፍርድ ቤት ውሳኔ ለመለያየት ማመልከት ትችያለሽ። በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ መስጠት የሚችለው በአካባቢሽ ያለው ፍርድ ቤት ነው። ልክ በቤተሰብ ፍርድ ቤት እንደሚደረገው ሁሉ በተለያዩ ነጥቦች ላይ ስምምነት ይደረጋል። ከተመሳሳይ ጾታ አጋርሽ ጋር በውሳኔው ካልተስማማችሁ ስምምነቱን ለማፍረስ ተለያይታችሁ አንድ አመት መቆየት ትችላላቹ። (በህጋዊ የወንድና የሴት ጋብቻ ግን 2 አመት ነው ተለያይቶ መቆየት ይቻላል) (Merkblatt Auflösung Eingetragene Partnerschaft)

### ከፍቅረኛዬ ጋር ትዳር ሳንመሰርት አንድ ላይ እንኖራለን፣ አሁን ግን መለያየት እፈልጋለሁ (ኮንኩቢናት)

ከፍቅረኛ ጋር ሳይጋቡ መኖር በህግ ላይ የተመሰረተ ትሥሥር አይደለም። ቢሆንም ማወቅ የሚያስፈልገን ነገር ያልተጋቡ ሰዎች ሲለያዩ የተለያየ ህጋዊ አመለካለት አለ። ልጆች ያላቸው ከሆኑ የፍርድ ቤት ጉዳዩ የልጆችን ሃላፊነት፣ እንዲሁም የልጆችን ጉብኝት በተመለከተ በልጆችና በአዋቂዎች ጥበቃ ባለስልጣን ይታያል። (kesb Zürich)
ለልጆቹ የሚታሰበውን መተዳደሪያ የሚወስነው በአካባቢያቸው ያለው ፍርድ ቤት ነው(BG Kanton Zürich)
ልጆቹን የሚንከባብከው አካል ህጋዊ ጋብቻ ከሌለው በሚለያዩበት ጊዜ የሚሰጠው መተዳደሪያ አይኖርም። በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚቆየው አካል መቆየት የሚችለው በእርሱ ፣ በአከራዩና በተለያየው ፍቅረኛው መሃከል በተደረገው የቤት ኪራይ ስምምነት ይወሰናል። ህጋዊ ጋብቻ ሳይፈጽሙ አብረው የኖሩ ሰዎች ሲለያዩ የሚኖረው ውጣ ውርድ አስቸጋሪ ስለሆነ የምክር አገልግሎት መጠየቅ ወይንም አንዲት ጠበቃ ማናገሩ ይበጃል።ፍቅረኛሽ በአንቺም ላይ ሆነ በልጆቹ ላይ በደል የሚፈጽም ከሆነ በህጉ መሰረት ጥበቃ እንዲደረግልሽ መጠየቅ ትችያለሽ።
(ስለ ደህንነት በራሪ ወረቀት)

ስለ ደህንነት በራሪ ወረቀት
ለትዳር ጉዳይ ጥበቃ ፍርድ ቤት የሚጠቅሙ
www.gerichte-zh.ch
የትዳር ጉዳይና ጥበቃ ፍርድ ቤት ፎርሙላ

ለድንገተኛ አደጋ አስፈላጊ የሆነ የህክምና ማስረጃ የሚገኝበት ቦታ
www.permanence.ch
Tel. 044 215 44 44

የጠበቆችና /የጠበቃ ማህበራት
www.zav.ch
www.anwaltskollektiv.ch
www.djs-jds.ch

የደህንነት ጥበቃ
የአደጋ ጊዜ የፖሊስ ስልክ ቁጥር 117
ጊዜያዊ የሴቶች ደህንነት ጥበቃ መኖሪያ ቤት
www.frauenhaus-schweiz.ch

ለተጎዱ ሴቶች እገዛ የሚያደርግ ተቋም
www.bif-frauenberatung.ch
www.frauennottelefon.ch
www.frauenberatung.ch

ለልጆች እገዛ የሚያደርግ ተቋም
www.kokon-zh.ch

BIF © አዘጋጅ

BIF Beratungsstelle für Frauen
ቢፍ (የ ሴቶች ምክ ር አ ገ ል ግሎት)
አ ቅራቢ Gegen Gewalt in Ehe und Partnerschaft
Postfach 9664, 8036 Zürich
Tel. 044 278 99 99
info@bif.ch
www.bif-frauenberatung.ch
PC 87-137016-4
**IBAN: CH32 0900 0000 8713 7016 4**

ጀር መን ኛ እ ር ማት Karin Ernst
ህ ጋ ዊ ምክ ር አ ገ ል ግሎት Brigit Rösli
ዲዛ ይን artischock.net
ትር ጉም Mary Schaffner-Kifle, weiss traductions genossenschaft

